# የ2002 ዓ.ም የሸካ ዞን አቅም ግንባታ መምሪያ

# 1ኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ

# ክንውን ሪፖርት

መስከረም 2002 ዓ.ም

ማ ሻ

# መ ግ ቢ ያ

የመንግስትን ፖሊሲዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አቅም ለመገንባት መልካም አስተዳደርና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን እውን ለማድረግ በአጠቃላይ ልማትን ለማፋጠን ይቻል ዘንድ ብቃት ያለው የሰው ሀይል ለማፍራት ጎታችና ኋላ ቀር አሠራር በመለወጥ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሠራር ዘይቤ መቀየስ ወሳኝ ነው፡፡

በዚሁ መሠረት መምሪያችን የ2002ዓ.ም ሰክቶሪያል ዕቅድ ነድፎ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለዉጥን በሁሉም የመንግስት ሰክተር መ/ቤቶች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ የቆየ ሲሆን የ1ኛ ሩብ ዓመት የዕቅድ ክንውን ሪፖርት የሁሉም የስራ ሂደቶች በአካተተ መልኩ አጠናቅሮ እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

# የ2002 ዓ.ም 1ኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ ክንውን ሪፖርት

1. ሪፖርት አቅራቢው :- ሸካ ዞን አቅም ግንባታ መምሪያ
2. ሪፖርቱ የሚሸፍነው ጊዜ ከሐምሌ 12001 እስከ መስከረም 30 2002 ዓ.ም

## በ ለውጥ ፕ/ፕ/ጥ/ት/የሥራ ሂደት የፕሮጀክት ዕቅድ ክትትልና ግምገማ የሥራ ክንውን

ሀ/ በ2ኛ ዙር መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ ሙሉ ትግበራ ክንውን

### 1. በ2ኛ ዙር ወደ ሙሉ ትግበራ ከመግባቱ በፊት የተከናወኑ ተግባራት

ደንብ ቁጥር 72/2001 ዓ.ም ለሰክተሮች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

ከዞን ሰክተር መ/ቤቶችና ኃላፊዎች ጋር ስለ 2ኛ ዙር /BPR/ አተገባበር ዙሪያ የግማሽ ቀን ውይይት በማድረግ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል፡፡ በየደረጃው ባሉ የወረዳና የከተማ አስ/ር አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች በሥሮቻቸው ላሉት ሰክተር ሀላፊዎችና ሠራተኞች ስለአጀማመሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ተሰርቷል፡፡

በደንብ ቁጥር 72/2001 መሠረት ደልዳይ ኮሚቴ ተዋቅሮ የሰራተኞች ድልድል ከተካሄደ በኋላ በመ/ቤታቸው ያልተደለደሉት በየደረጃው ባለው አማራጭ ግረ ሀይል እንዲደለደሉ የተደረገ ሲሆን ሥልጠና ያገኙ የአብዛኛዎቹ መ/ቤቶች በድርጊት መርሀ - ግብሩ መሠረት ከመስከረም 4/2002 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ሙሉ ትግበራ ገብተዋል፡፡

2. የሙሉ ትግበራ ሂደት ሲጀመር አስተባባሪዎችና ፈፃሚዎች የሚያስፈልጋቸውን ግብዓት እንዲያዘጋጁ ውይይት ተደርጓል።
3. በሥራ ሂደቱ ትግበራ ማኑዋልና ቲም ቻርተር ላይ ሥልጠና ሳይወስዱ የተካተቱ ሠራተኞች አሉ። ምክንያቱም ሥልጠናው የሚሰጠው በየሰክተር ቢሮዎች በመሆኑ የስልጠና ጊዜ ወጥ ባለመሆኑ ነው።
4. በ2ኛ ዙር /BPR/ ሠራተኞች ድልድል አፈፃፀም ላይ የተነሳ ቅሬታና ተቃውሞ የለም፡፡
5. አስተባባሪዎቹም ሆነ ፈፃሚዎቹ በደንብ ቁጥር 72/2001 መሠረት የሙያ መስመራቸው ተገቢነት መሠረት የተመደቡ ሲሆን በድልድል የታቀፉ

ሠራተኞች አዲሱ የስራ ሂደት ምደባ ደብዳቤ ላይ የሥራ መደቡ መጠሪያና የደመወዝ መጠን ተገልፆላቸዋል በዚሁ መሠረት በድልድል የታቀፉት ሠራተኞች ብዛት 384 ናቸው

የሰራተኞች አመዳደብ በትምህርት ደረጃ ሲታይ

- ከሠርተፊኬት በታች 9
- ሠርተፊኬት 82
- ዲፕሎማ 227
- ዲግሪ 64
- ማስትሬት 2 ናቸው፡፡

6. በድልድል ያልታቀፉት ሠራተኞች ብዛት 77 ናቸው

ይህ በትምህርት ደረጃ ሲታይ

- ከሠርተፊኬት በታች 26
- ሠርተፊኬት 51 ሲሆኑ ይህም በደንብ ቁጥር 72/2001 የአፈፃፀም መመሪያ መሠረት ይተገበራል፡፡

7. የቢሮ አደረጃጀትን በተመለከተ

በ2ኛ ዙር ወደ ሙሉ ትግበራ ከገቡት ሰክተር መ/ቤቶች ውስጥ ከዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትና አስተዳደር ጽ/ቤቶች በስተቀር ሁሉም ሰክተር መ/ቤቶች በደባል ቢሮ ስለሚሰሩ ለትግበራው ምቹ ቢሮ ባይኖርም በየሥራ ሂደቱ አስተባባሪዎችና ፈፃሚዎች በአንድ ላይ ሆነው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

8. ትግበራውን የተሳካ ለማድረግ የዞን አስተዳደር ጽ/ቤት ለ13 ዞን ሰክተር መ/ቤቶች 411400 ብር የተወሰኑ ባለሙያዎች ቅጥር እንዲፈፅሙ ድጋፍ አድርጓል፡፡

## 9. በአንደኛ ዙር ወደ ሙሉ ትግበራ የገቡ ሰባት ሰክተር መ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል በተመለከተ

- በዞን ሰክተር መ/ቤቶች እና በወረዳና ከተማ አስተዳደር 2 ጊዜ ድጋፋዊ ክትትል በማድረግ
- በዕቅድ ዝግጅት ዙሪያ በመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ አተገባበር የትኩረት አቅጣጫ ዙሪያ

- ስለ ዕለታዊ፣ ሳምንታዊ ሥራ ክንውን ግምገማ፣
- የሰው ሀይል ማሟላትን በተመለከተ
- ለስራ ሂደት አስተባባሪዎች ቲተር ተዘጋጅቶላቸው ደብዳቤዎችን በራሳቸው እንዲፈርሙ ስለ ቢሮ አደረጃጀት፣ ባጅና መታወቂያ አዘገጃጀት፣
- በአስተባባሪዎችና በፈፃሚዎች መካከል መኖር ስለሚገባ የሥራ ግንኙነት
- ስለ መረጃ አደረጃጀት በየጊዜው ድጋፋዊ ክትትል ተደርጓል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን በወር ሁለት ጊዜ በየ 15 ቀን ድጋፋዊ ክትትል ለማድረግ ከግብርናና ገጠር

ልማት መምሪያ፣ ከት/ት መምሪያ፣ ከጤና መምሪያ፣ ከን/ኢ/መምሪያና ከታክስ አስተዳደር ጽ/ቤቶች ጋር የ 6ወር የስምምነት ሰነድ ፊርማ ተካሂዷል፡፡

10. ከ9 ሰክተር መ/ቤቶችና ከ16 ጽ/ቤቶች የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች ጋር በዓመታዊ ዕቅድ ዝግጅት ዙሪያ ግብረ - መልስ ውይይት ተካሂዷል፡፡
11. የመ/ቤቱ ስትሪንግ ኮሚቴ በየሳምንቱ እየተገናኘ በ BPR አፈፃፀም ዙሪያና ባጋጠሙ ችግሮች እንዲወያዩ አጠቃላይ ሠራተኞች ደግሞ በወር አንድ ጊዜ ተገናኝተዉ ዉይይት እንዲያደርጉ ለመ/ቤቶች ድጋፍ ተደርጓል፡፡
12. የዞኑ አቅም ግንባታ ባለሙያዎች አንድ ዙር ለወረዳና ከተማ አስተዳደር አቅም ግንበታ ጽ/ቤቶች አንድ ጊዜ ሙያዊ ድጋፍ አድርገዋል እንዲሁም የ2002 የዕቅድ ውል ስምምነት ሠነድ ተፈራርመዋል፡፡ ከዚህም ሌላ የዞኑ አቅም ግንባታ መምሪያ ኃላፊና ባለሙያዎች የ3ቱ ወረዳና የ2ቱ ከተማ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች አፈፃፀምን ገምግመው ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት የአፈፃፀም አቅጣጫና በትኩረት ነጥቦች ላይ ግንዛቤ አስጨብጠዋል፡፡

# <u>የገጠር ቀበሌ መላካም አስተዳደር</u>

ምርጥ ልምዶችን ከማስፋፋትና ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በግልም ሆነ በወል ዲሞክራሲያዊ በሆነ ምልኩ እንዲተገበሩ ከቀበሌ አመራር መዋቅር እስከ ልማት ቡድን ያሉት አመራሮች በየጊዜው እየተፈተሹ በሞዴሎች እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የአመራር አካት ቀልጣፋ አገልግሎት እኒዲሰጡ ትምህርት ተሰጥቷል፡፡

1. በአንድራቻ ወረዳ ሞዴል አመራርና ሞዴል ቀበሌ በመለየትና በወረዳ ምክር ቤት ጉባኤ

የመሸለም ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚሁ መሠረት በወረዳው ውጥ ከሚገኙት 15 ቀበሌዎች በተሻለ

ወይም በላቀ አፈፃፀማቸው የተመረጡት

1. ገቲባ ቀበሌ
2. ቱግሪ ቀበሌ
3. ዮክጭጨ ቀበሌ

ሲሆኑ ለቀበሌዎችና ለ3 ቱ ቀበሌ ሊቃነ መናብርት ሽልማት ተሰጥቷል፡፡

2. የማሻ ወረዳ የ 19 ቀበሌዎች 152 ከሚሆኑ የአመራር አካላት ጋር በየወሩ ውይይት በማድረግ

አፈፃማቸውን ገምግሞዋል፡፡ በተቀመጠው የምርጫ መስፈርት መሰረትም ከ19 ቀበሌዎች

ሦስት ቀበሌዎችን በሞዴልነት መርጧል፡፡ በዚሁ መሠረት በአፈፃፀማቸው ደረጃ ተሰጥቷቸው

የተመረጡት ቀበሌያት

- በቶ ቀበሌ
- የጶ ቀበሌ
- ኬዎ ቀበሌ ናቸው

3. የኢንስፔክሽን አደረጃጀትን በተመለከተ በአንደኛው በ15ቱም የገጠር ቀበሌዎች የእንስፔክሽን

ቡድን የተቋቋመ ሲሆን በ2 ወረዳ ግን ለማቋቋም በዝግጅት ላይ ናቸው፡፡

4. የገጠር ቀበሌ ሥራ አስኪያጆችን በተመለከተ ገጠር ቀበሌዎች ተቋማዊ አሰራር

እንዲኖራቸው የአመቱን እቅድ አቅደው እንዲንቀሳቀሱ የተደረገ ሲሆን በየጊዜውም
ድጋፋዊ ክትትል እየተደረገ ግብረ መልስ እየተሰጠ እንዲጠናከሩ እየተደረገ ነው፡፡ ከዚህ
ጎን ለጎን በብቃት ማነስና በራሳቸዉ ፍላጎት በለቀቁት አራት የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች
ምትክ ቅጥር በመፈፀምና ለ7 ተካታታይ ቀናት ሥልጠና በመስጠት በማብቃት ሥራ
እንዲጀምሩ ተደርጓል። እንዲሁም ጥሩ አፈፃፀም ያሳዩትን ሥራ አስኪያጆችን የመሸለምና
የማበረታታት ሥራ ተሰርቷል።

- በከተማና በቀበሌ ደረጃ የመልካም አስተዳዳር ፓኬጅን ተግባራዊ ለማድረግ በየቀበሌው ሥራ አስኪያጆች ተቀጥረው በአሰራር ዙሪያ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጎ ወደ ሥራ ተገብቷል።

## ሐ. <u>የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያን በተመለከተ</u>

## የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራምን በተመከት

- ቀደም ሲል በአንድ ወረዳ ላይ ብቻ ይካሄድ የነበረው ተዘዋዋሪ ችሎት በተጨማሪ በአንድራቻ ወረዳ ላይ እንዲካሄድ የወረዳ ፍ/ቤቶችም የማሕበራዊ ፍ/ቤቶችን አቅም እንዲያጎለብቱ በተደረገዉ ድጋፋዊ ክትትል ከዞን ከ/ፍ/ቤት ጋር በስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ የከተማ ማ/ፍ/ቤቶችም ተደራጅተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡
- የዞኑ ከ/ፍ/ቤት በ2ኛ ዙር ሙሉ በሙሉ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለዉጥን ተግባራዊ በማድረግ ላይ የሚገኝ ሲሆን አቤቱታ የመስማትና የመወሰን የሥራ ሂደት ምቹ ቢሮ በማዘጋጀትና የተሟላ የሰዉ ኃይል በመመደብ ወደ ተግባር የገባ ሲሆን በአጠቃላይ በዋናና በደጋፊ የሥራ ሂደት የሰዉ ኃይሉን 72.41% በማድረስ አርአያነት ያለዉ ሥራ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

## መ. ፍትህና ፀጥታን በሚመለከት

- በ BPR አተገባበር ለመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለዉጥ ምቹ የሆነ ቢሮ ስለሌላቸዉ አዲስ እየተገነባ ባለው ቢሮ ለስራ ሂደቶቹ በማመቻቸት ላይ ይገኛል (ዞን ፍትህ)
- የሰው ሀይላቸውን ለሟሟላት ቅጥር ለመፈፀም 54156.60 ብር አስፈቅዷል (ዞን ፍትህ)

## ሠ. የፐሊስ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራምን በተመለከተ

- የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ ኅብረተሰቡ በወንጀል መከላከል እንዲሳተፍ የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ማጠናከር እና ማደራጀት ዙሪያ ከዞን ፖሊስ መምሪያ ጋር ውይይት በማድረግ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ከዚህም ሌላ በገጠር ቀበሌያት የወንጀል መከላከልን ሥራ በስፋት ለመስራት ቀበሌዎችን በየ ክላስተር በማደራጀት ሁለት ሁለት ፖሊሶች እንዲመደቡ ተደርጓል፡፡ ከአንድ ወረዳና ከተማ አሰ/ር ጽ/ቤቶች በደረሰን ሪፖርት ለ4905 የሕ/ሰብ ክፍሎች ስለ ኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ትምህርት ተሰጥቷል::

## ረ. የማረሚያ ተቋም ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም

1. የታራሚዎችን ሰብዓዊ መብት ከመጠበቅ አኳያ
   - ደረጃውን የጠበቀ የእስረኞች ማደሪያ በፆታ ተለይቶና ንፅህናው ተጠብቆ የቴሌቪዥን አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡
2. የማረሚያ ቤቱ የመና አቅርቦትና ግዥ ግልፀኝነትን የተከተለ ሲሆን ይኸውም እስረኞችን ያጣመረ ኮሚቴ በማዋቀርና በግልፅ ጨረታ በማከናወን ላይ ይገኛል
3. የታራሚዎች ህክምና አሰጣጥ በአከባቢው ጤና ጣቢያ የሚታከሙ ሲሆን ዘላቂነት ባለው መልኩ የህክምና ስርዓት ለመዘርጋት የራሳቸውን ክሊኒክ በመገንባት ላይ ይገኛሉ
4. ታራሚዎች የእስር ጊዜያቸውን ጨርሰው ሲወጡ መልካም ዜጋ ሆነው ተቀርፀው እንዲወጡ ለማድረግ

- የተለያዩ የእደ- ጥበብ ሙያዎችን የጓሮ አትክልቶችን አመራረት እንዲማሩ ተደርጓል፡፡
- ከዚህ ጎን ለጎን የእንጨት ማሽን በመግዛት ሙያተኞችን በመቅጠር ታራሚዎች በዚህ መስክ እንዲሰለጥኑ እየተደረገ ነው

5. ከ BPR አተገባበር አኳያ በቂና ምቹ ቢሮዎችን በማደራጀትና የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በማደረጃት ትግበራው እንዲሳካ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ እስካሁን ያለው የሰው ሀይል 35% ብቻ መሆኑና የሚቀጠሩትም ሰራተኞች ለቀው ስለሚሄዱ ችግር ገጥሟቸዋል፡፡

## የኢኮቴ መ/ል/አቅ/አገ/የሥራ ሂደት

# የ2002 ዓ.ም 1ኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ ክንውን ሪፖርት

የሥራ ሂደቱ በ2002 ዕቅድ ዘመን በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለዉጥ ትግበራን በአዳዲስ አሠራር ፣ ቴክኖሎጂን በተከተለ መልኩና እንዲሁም ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለደንበኞቹ መስጠትን እንደ ቁልፍ ተግባር አድርጎ በማቀድ በ2002 በ1ኛ ሩብ ዓመት የሚከተሉት ተግባራት አከናዉኗል፡፡

1. በመጀመሪያ ዙር BPRን ተግባራዊ ላደረጉ ሰክተሮች መሠረታዊ የኮምፒዉተር ሥልጠና ለ36 የዞን ሰክተር ሠራተኞች ለመስጠት ታቅዶ
   2.2.**ወንድ** 23

   **ሴት** 5 በጠቅላላዉ 28 ሰዉ የተያዘለትን የሥልጠና ሰዓት በማጠናቀቁ የምረቃ ሥነ - ሥርዓት በማዘጋጀት የመጀመሪያ ዙር ሥልጠና እንዲያበቃ ተደርጓል፡፡

   3.3.ለተመራቂ ሠልጣኞች ሠርትፊኬት በማዘጋጀት ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን የማሻ ወረዳ ለ11 የአንድራቻ ወረዳ ደግሞ ለ40 አመራሮችና ባለሙያዎች መሠረታዊ የኮምፒዉተር ሥልጠና መስጠት የጀመረ ሲሆን የየኪ ወረዳም ዝግጅቱን በማጠናቀቅ ወንድ 7 ሴት 5 በድመሩ ለ12 አመራሮችና ባለሙያዎች ሥልጠናዉን መስጠት ጀምሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የማሻ ከተማ አስተዳደር ዝግጅቱን አጠናቆ ለ10 ባለሙያዎች ሥልጠናዉን ለመጀመር ቢዘጋጅም የመብራት ችግር ስላጋጠመዉ ሥልጠናዉን እስካሁን ድረስ ለመጀመር አልቻለም፡፡

2. <u>የገጠር ሽቦ አልባ ስልኮች (Rural Connectivity)በተመለከተ</u>

   2.2.በ3ቱ ወረዳዎች ዉስጥ የሚገኙ 56 ቀበሌዎች ሽቦ አልባ ስልክ ያላቸዉ በቁጥር 45 እና የሌላቸዉ 11 ተለይተዉ መረጃቸዉ ለክልል ተላልፏል፡፡የ2 ገጠር ቀበሌዎች ሽቦ አልባ ስልኮች ብልሽት

ተፈጥሮ ከቴሌ ባለሙያዎች ጋር በመሆን የማስተካከያ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ (አንድራቻ ወረዳ)

## 3. <u>የቪዲዮ ኮንፈረንሲንግን በተመለከተ</u>

3.1. የማሻ ወረዳ ቪዲዮ ኮንፈረንሲንግ ከሌሎች ወረዳዎችና ልዩ ወረዳዎች ጋር

ግንኙነት ያደርጋል፡፡ ይህም ከላይ የተገለፁት ወረዳዎች ቪዲዮ ኮንፈረንሱ ክፍት

ሲሆን ማለት ነዉ፡፡ አገልግሎት አሰጣጡን ስንመለከት ከደንበኞች ጥያቄ

አልቀረበላቸዉም ቢቀርብላቸዉም የኦዲየ(የድምጽ) መቆራረጥ ስላለ ችግር ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪ ደግሞ የየኪና የአንድራቻ ወረዳ ደግሞ ከላይ ከተገለፀዉ ጋር ተመሣሣይነት ሲኖረዉ ለየት የሚያደርገዉ ግን የቪዲዮና የኦዲዮ (የምስልና የድምፅ) መቆራረጡ ነዉ፡፡

4. ዩፒኤስ (UPS) ን በተመለከተ

4.1. በዞን ሰክተር ያሉ የዩፒኤስ (UPS) በዞን 3 በወረዳዎች 12 በጠቅላላው 15

ዩፒኤስ (UPS) ከዞን እስከ ከተማ አስተዳደር ሰክተር ድረስ ያለውን በብዛትና

በሞዴል ተለይቶ ለክልል አቅም ግንባታ ቢሮ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡

## 5. <u>የመምሪያውን የድህረ ገጽ (ዌብ ሳይት) በተመለከተ</u>

5.1. የሸካ ዞን አቅም ግንባተ መምሪያ የድህረ ገጽ በተሳካ መልኩ እንዲሰራ የመምሪያውን የተሟላ መረጃ በማሰባሰብ ለክልሉ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡

## 6. <u>የኔት ወርክ ዝርጋታን በተመለከተ</u>

6.1. እስካሁን ባለዉ ሁኔታ ኔት ወርክ ለመዘርጋት ምቹ ሁኔታ አልተፈጠረም ማለትም የተለያዩ መሟላት የሚገባቸዉ ማቴሪያሎች ስለሌሉ ሥራዉ ልሠራ አልቻለም፡፡ ለወደፊት ግን ማቴሪያሎች

ተሟልተዉ ሥራዉ የሚቀጥልበትን ሁኔታ መምሪያዉ እንዲያመቻች ጥረት በማድረግ ላይ እንገኛለን፡፡

## 7. ኢንተርኔትን በተመለከተ

በሸካ ዞንና ወረዳ ኢንተርኔት ያላቸዉ ሰክተር መ/ቤቶች ሥም ዝርዝራቸዉ እንደሚከተለዉ ተዘርዝሯል፡፡

### 7.1. ከዞን ሰ/መ/ቤቶች

- የሸካ ዞን ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ
- የሸካ ዞን ጤና መምሪያ
- የሸካ ዞን ፋይ/ኢ/ል/መምሪያ
- የሸካ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት
- የሸካ ዞን አቅም ግንባታ መምሪያ

### 7.2. ከወረዳ ሰ/መ/ቤቶች

- ማሻ ወረዳ ICT
- ማሻ ከተማ ጥቃቅንና ንግድ ኢንዱስትሪ ኢንተርፐራይዝ ማደራጃ
- ማሻ ከፍ/2ኛ ደረጃ ት/ቤት
- የየኪ ወረዳ ICT
- አንድራቻ ወረዳ ICT

## 8. የጥገና አገልግሎትን በተመለከተ

8.1. ለሚከተሉት 5 የዞን ሰ/መ/ቤቶች ኮምፒዉተርና ፐርንተር በዞኑ የኢኮቴ ባለሙያዎች ጥገና ተደርጎአል፡፡ እነሱም፡-

- ለዞን ትምህርት መምሪያ (ኮምፒዉተርና ፐርንተር ጥገና)
- ለዞን ባህልና ማስታወቂያ መምሪያ (ኮምፒዉተርና ፐርንተር ጥገና)
- ለዞን ግ/ገ/ል/ጽ/ቤት (የኮምፒዉተር ጥገና)
- ለዞን ለማረሚያ ተቋም(ኮምፒዉተርና ፐርንተር ጥገና)
- ለዞን ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት(ኮምፒዉተር ጥገና)

8.2. የየኪ ወረዳ ባለሙያ ለ3 የወረዳ ሴክተሮች 3 ኮምፒዉተሮችንና 3 ፕርንተሮችን ጠግኗል፡፡ እንደዚሁም የአንድራቻ ወረዳ የኢኮቴ ባለሙያም ለ2 የገጠር ቀበሌዎች ሽቦ አልባ ስልኮች ብልሽት ገጥሞአቸዉ ከቴሌ ጋር በመሆን የጥገና ሥራ ሠርተዋል፡፡ ከከተማ አስተዳደሮች የማሻ ከተማ አሰ/ር አቅም ግንባታ ባለሙያም 1 ፋክስና አንድ ኮምፒዉተር ለማሻ ከተማ ፋይናንስ የጥገና አገልግሎት ሰጥቷል፡፡

## 9. ድጋፍና ክትትልን በተመለከተ

9.1. በየወረዳ እና በየከተማ አስተዳደር ሥር የሚገኙ የአይሲቲ መሳሪያዎችን ክትትል ከማድረግ አንፃር የተለያዩ ህጋዊ ያልሆኑ ባለሙያዎች መሳሪያዎችን በመነካካት ብልሽት እንዳያጋጥመው ከክልል በተላከው መመሪያ መሠረት ለወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች በተደጋጋሚ ጥብቅ መመሪያ እንዲተላለፍላቸው ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ወረዳዎችን ከመደገፍ አንፃር ብዙ ጊዜያችንን በመሠረታዊ የኮምፒዉተር ሥልጠና ላይ ያሳለፍን ስለሆነና በየወረዳዉ ወርዶ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ሰዓት ያጠረን ስለሆነ አሁን ባለዉ ሁኔታ የቼክ ሊስት ዝግጅት ተጠናቆ ድጋፍ ለመስጠት ዝግጅት ላይ እንገኛለን፡፡

9.2. በሁለት ሴክተር ለሚገኙ ለ30 የመንግስት ሰራተኞች የኢኮቴ ባለሙያዎች የደረት ባጅ በኮምፒዉተር በመሥራት በአነስተኛ ወጪ እንዲጠቀሙ አድርገዋል፡፡ (ማሻ ወረዳ)

9.3. ለ3 የወረዳ ሴክተሮች በኢኮቴ ባለሙያ ሶስት ኮምፒዩተሮች እና ሶስት ፕሪንተሮች ጥገና ተደርጎላቸዋል፡፡(የኪ ወረዳ)

9.4. ለማሻ ከተማ መረጃ ማዕከል አንድ ፕሪንተር እንዲገዛ ተደርጓል፡፡

10. <u>የማህበረሰብ መረጃ ማዕከልን በተመለከተ</u>

ይህ የማህበረሰብ መረጃ ማዕከል በሸካ ዞን ማሻ ከተማ ዉስጥ ብቻ የሚገኝ ሲሆን በማህበረሰቡ መረጃ ማዕከል ዉስጥ የታቀፉት አባሎች በማዕሉ የሚፈልጉትን ሥራ ሠርተዉ የዕለት ገቢያቸዉን ለማሳደግ የተለያዩ መሰናክሎች ገጥመዋቸዋል፡፡ እነዚህም ችግሮች፡-

1ኛ. ለመረጃ ማዕከሉ የተሰጠ ኢንተርኔት ፓስወርድ መጥፋት እንደገና ቶሎ ተስተካክሎ ያለመምጣት

2ኛ. መብራት ኃይል ያለመኖር(በየጊዜዉ መቆራረጥ ) እና ለዚህም ምትክ የሚሆን ጀነሬተር መግዛት

አለመቻል

3ኛ. ኮምፒዉተሮች በቁጥር ማነስ

4ኛ. መረጃ ማዕከሉ በከተማ ዉስጥ ፊት ለፊት የሆነ ቦታ ያለማግኘት ችግሮች ናቸዉ፡፡

# 11. <u>ያጋጠሙ ችግሮች</u>

## 11.1. <u>ሥልጠናዉን በተመለከተ</u>

- ቀላልና መካከለኛ ጥገና የሚፈልጉ ማሽኖች በየሰክተር መ/ቤቶች ቢኖሩም ከኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ ያገኘነዉ

ዕዉቀት በቂ ባለመሆኑ እነዚህን ችግሮች ሙሉ በሙሉ ለመቅረፍ ያለመቻል ፣

- ለጥገናዉ ሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች ያለመሟላት ለምሳሌ፡-

1. የተሟሉ የጥገና ቱል ኪቶች (TOOLKITS)
2. መለዋወጫዎች እንደ (HARD DISK) እና ሌሎችም
3. የተለያዩ ሶፍት ዌሮች

- <u>ማቴሪያልን በተመለከተ</u>

1. በቂ የሆኑ ለሥልጠና የሚሆኑ ኮምፒዉተሮች ያለመኖር
2. ያሉትም ኮምፒዉተሮች 2nd ሀንድ በመሆናቸዉ ሲስተማቸዉ በየጊዜዉ ፕሮግራሞችን

ስለሚያጠፋ (PROGRAM FAIL) እያደረጉ በማስቸገራቸዉ ለሥልጠናዉ ሂደት ላይ ከፍተኛ

ችግር አጋጥሟል፡፡

3. ለኢኮቴ የሥራ ሂደት (ICT DEPARTMENT) የተላኩት ላፕ ቶፖች በሥራ ሂደቱ እጅ

ያለመሆን፣

## የመፍትሔ ሐሳቦች

- **ከዚህን በፊት ያጋጠሙንን ችግተሮች ለመቅረፍ የሰጠናቸዉ መፍትሔዎች**

- ባሳለፍናቸዉ የሥራ ጊዜያት ሥልጠና በከፍተኛ የሚያስፈልገን ቢሆንም በተቻለን መጠን አነስተኛ የጥገና አገልግሎት በመስጠትና ባለን አነስተኛ ማተርያል በመጠቀም ሥራዉን ሠርተናል፡፡

- የማሽነሪዎችን ጥገናን በተመለከተ ከአንዱ ማሽን ወደ ሌላዉ ማሽን በማዘዋወር ማሽኑ እንዲንቀሳቀስ አድርገን በተጨማሪም ማሽኑ ሶፍት ዌር ሲያስፈልገዉ ከቢሮዉ ማግኘት ስላልተቻለ በግላችን እየገዛን ማሽኑ ሥራ ላይ እንዲሆን አድርገናል፡፡

- ለሥልጠናዉ የተገዙ ኮምፒዉተሮች በጣም የቆዩ ሞዴሎች በመሆናቸዉ ፕሮግራሞች በየጊዜዉ ፌል እያደረጉ ያስቸግራሉ በተጨማሪም ኮምፒዉተሮች በቁጥር አናሳ በመሆናቸዉ ሥልጠናዉን በአግባቡ ለመስጠት አስቸጋሪ ቢሆንም ያለዉን ችግር በመጋፈጥ ሥልጠናዉ በተሳካ መልኩ እንዲጠናቀቅ ተደርጓል፡፡

- **ለወደፊቱ መፍትሔ ይሆናሉ ተብለዉ የሚጠበቁ እሳቤዎች**

- ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ የማሽኖች ጥገና ለመስጠት ከኮሌጆችና ከዩኒቨርሲቲዎች ያገኘናቸዉ ዕዉቀቶች በቂ ስላልሆኑ ይህንኑ ችግር በመገንዘብ ቴክኒካል የሆነ ሥልጠና የተለያዩ ማሽኖችን በተመለከተ (ኮምፒዉተር፣ ፕርንተር፣ ፎቶ ኮፒ ፣ ፋክስ፣ ቪዲዮ ኮንፈረንሲንግና) ከዚህም ተጓዳኝ የሆኑትን ተከታታይነት ያለዉ ሥልጠና ቢሰጠን ችግሩ ይቀረፋል ብለን እናምናለን።

- ለማሽኖች ጥገና የሚያስፈልጉ የተለያዩ መለዋወጫዎችን ብቀርብልን የወደፊት መፍትሔ

ይሆናል ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተለያዩ አዳዲስ የሚወጡ ሶፍት ዌሮች በክልሉ የICT

የሥራሂደት ባለቤት በኩል ማግኘት ቢቻል መፍትሔ ይሆናል፡፡